በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association




የተሰጠ መግለጫ

ሕዳር 16ቀን 2007ዓ.ም

**ጀግኖችን እያሰብን የበኩላችንን እንወጣ!!**
**በመስዋዕትነት ነፃነት ይረጋገጣል፤ ሰላም ይሰፍናል።**

መምህር የኔሰው ገብሬ በዳውሮ ከተማ ነዋሪና ትጉህ መምህር ነበር። እንደማንኛውም አገር ወዳድና የወገን ተቆርቋሪ እርሱም የወያኔ/ኢህአዴግ ሥርዓተ መንግሥት በሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን ገደብ የለሽ ሰቆቃ መቀበል ባለመቻሉ ፣ በአንፃሩ በተቃውሞ አቋሙን በአደባባይ የሚገልጽና ይህ እኩይ ድርጊት እንዲቆም ታግሎ ለማታገል በጽናት ስለቆመ የሥርዓቱ ሰለባ ሆነ። እስራቱና እንግልቱ አልበቃ ብሎ ከሥራ መደቡም ተገለለ ። በዚያው ላይ ፍትህ ለማግኘት የሚያስብ ሕሊናና የሚሰማ ጆሮ እንደሌለ ተረድቶ ለአሰቃዩትም ለአጠቃላይ ሕዝቡም መራር መልእክት ያስታላልፋል ብሎ ያሰበውን መስዋዕትነት መርጦ ራሱን በጋዝ አንድዶ ሕዳር 1 ቀን 2004 ዓ.ም መስዋዕት ሆነ። ይህ ተግባሩ ቀደም ሲል ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ሉዓላዊነት ፣ ለመምህሩ መብትና ጥቅም መከበር ሲታገሉ መስዋዕት የሆኑትን፣ በእስራት የማቀቁትን፣ ከእናት አገራቸው ተሰድደው በባዕድ አገር ያለውዴታቸው የእንግልትና የናፍቆት ኑሮ የሚገፉትን መምህራን፣ የሙያ ማህበሩ የኢመማ መሪዎችን፣ ደጋፊዎቻቸውንና ተባባሪዎቻቸውንም የሚያስመካ አንጸባራቂ መስዋዕትነት ሆኖ አልፏል። መቼም ቢሆን ነፃነት ያለመስዋዕትነት ተገኝቶ አያውቅም። በሕዝቡ ጫንቃ ላይ ተፈናጦ የሚገኘውን ጨካኙን፣ ዘረኛውን፣ ግፈኛውን፣ ገዳዩንና አገር አጥፊውን ወያኔን ቆርጠን በመታገልና በመስዋዕትነት ብቻ ነው ነፃነታችንን ልናገኝ የምንችለው።
በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ መምህር የኔሰው ገብሬ ራሱን መስዋዕት ያደረገበትን ሕዳር 1 ቀን በክብር ያስታውሳል፤ ቀጥሎ ያለውንም ግጥም በመታሰቢያነት ያቀርባል።

ከአመታት በፊት - ከአምናው ከአቻምናው፣
ከጻፍን-ካነበብነው- ካየን ከሰማነው፣
አጀብ ነው ይገርማል- ያሁኑስ የጉድ ነው ፣
የመምህሩ ትግል ልዩ ነው ከወትሮው፣
ከሥራ መባረር-መታሰር ግድያ---ሁሉን ተጋፈጥነው፣
ይኸን ችሎ መኖር- ሕይወት ትርጉም የለው፣
ብሎ ወሰነና- ቆራጥ ሆኖ አቅዶ፣
ጋዙን አርከፍክፎ- ራሱን አንድዶ፣
ሕዝብን አስተማረ - ጠላት እንዲያጠፋ ዱር ገድል አሳዶ።
የኔሰው ገብሬ - የሙያ አጋሬ ፣



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

ልበልህ ሰንደቁ - ልበልህ አጅሬ፣
ቆራጥነት ካንተ- አልፍ አእላፍ ይማራል፣
ጠላት ድባቅ መትቶ ቆሞ ይፎክራል፣
ከድልም በኋላ አንተን ይዘክራል።
የኔሰው ሳተና፣
ቆራጡ ቆፍጣና፣
ድፍን ያገሩን ሰው - በአንክሮ አስደመመ፣
መታየት ጀምሯል - የተሰፋ ቡቃያ እየለመለመ፣
ሕዝቡም ተነሳስቷል - ትግሉን ሊቀላቀል በአንድ እየተመመ።
መስሎ ማደር ሲችል - ሳይጎድል ምቾቱ፣
ሕሊናው ለድሎት ባለመገዛቱ፣
ፍትህ አጥቶ ድሎት አረ ምናባቱ፣
ስብዕና አጥቼ - እንዴት ልሁን ገልቱ፣
ወገኔስ ተዋርዶ - ተገፍቶ-ተገፍቶ - እስከግፍ ዳርቻ፣
አገር ቅርጫ ሆና - ጠላት ተሳለቀ - በመንጋ ዱርየ ሆነን መጫወቻ፣
የቀደመው ታሪክ - የአርበኝነት ገድል ሆኖ መዘባበቻ፣
የኔሰው ቆራጡ ራሱን የሰዋው-ይኸንን ነግሮን ነው መሰነባበቻ።
እንደቀድሞው ሁሉ ለወገን መቆም ዘብ፣
ታሪክን አድሰን እንድንገነዘብ፣
እንዳናፈገፍግ - እንዳናፈነግጥ፣
የየኔሰው ገብሬ - መሰዋዕትነቱ አስሮናል እንደልጥ።
ግና ከዚህ አንፃር በስመ አስተማሪ ለጥቅም ስትሉ፣
ከመሰመር ወጥታችሁ የምትባትሉ፣
ቀኑ እየመሸ ነው ይኸን ልብ በሉ፣
የፍርድ ቀን ሳይደርስ ፣
ጉድ አቧራ ሳይጨስ፣
ማረኝ የአገሬ ሕዝብ- ማረኝ ኢመማ፣
ብላችሁ ቅረቡ ( ቁረቡ) በዚህ እንስማማ።
አያችሁ!አያችሁ! አያችሁ!
የሚያስብ አእምሮ ሕሊና ካላችሁ፣
የየኔሰው ገብሬ መስዋዕትነቱ - ከበቂ በላይ ነው የሚያስተምራችሁ።
በቆየው ታሪኩ ሆኖ እንደተገኘ የለውጥ ፊታውራሪ፣
የባሰ መጥቶብን - ሕዝብን አሸባሪ፣
ከመሐል እስከዳር - አገርን ቸርቻሪ፣
በዚህ ወቅት እኮ ነው - ለሕዝብ ፀንቶ መቆም ድርሻው ያስተማሪ።
ምንድነው ሚስጢሩ - የሕይወት ትርጉሙ፣
አትብሉ - አትጠጡ፣
በችግር ተቀጡ፣
ዝም! ጭጭ! እንድንል - ብሶት ላናሰማ ጠብቆን ልጓሙ፣
ጠላቶቻችንም ከቅርብና ከሩቅ በእኛ ላይ ሲያድሙ፣
ቢቻል ባንድ ጉድጓድ ሊቀብሩን ሲያሴሩ፣
በፍርሃት ቆፈን ተይዘን ካልሆነ ምንድነው ነገሩ?!
በቡድን ወይ በግል፤
ትግሉን እናጋግል፣
ይህንን ሥርዓት ከስሩ እንመግል፣
ሰበብ ማብዛት ይቅር እንከተል ጀግና፣
የትግል ተምሳሌት - ብዙ የኔሰዎች ይፈጠራሉና!!

***ጀግናን ጭዳ ማድረግ ይቁም!!***
***በገዳዮች ላይ እንነሳ!!***